# ከኢትዮጵያ ሙስሊሞች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

እሁድ መስከረም 1/2009 አዲስ አበባ/ኢትዮጵያ

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ፣ በጣም አዛኝ በሆነው!

**ውድ የአገራችን ህዝቦች ሆይ!**

አገራችን ኢትዮጵያ ያሳለፈችው የረጅምና የአጭር ጊዜ ታሪክ አካል የሆነው የህዝብ ስልጣን ባለቤትነት አለመከበር፣ የእኩልነትና የእኩል ተጠቃሚነት መርህ አለመተግበርና በአጠቃላይ ዜጎችን ሁሉ ሊያሳተፍ የሚችል ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እጦት አሁን ላለንበት እጅግ አሳሳቢ ወቅታዊ ሁኔታ እንዳበቃን ለማንም ግልፅ ነው፡፡ በመሆኑም ህዝብ የመብትና የነፃነት ጥያቄውን አንግቦ አደባባይ የወጣበትና ስርዓቱን የተቃወመበት፣ በብዙ የአገራችን ክፍሎችም እስከ ህይወት መስዋእትነት እየተከፈለ ያለበት፣ በአገር አቀፍ ደረጃም ከፍተኛ ውጥረት የነገሰበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን፡፡

ይህ ህዝባዊ ተቃውሞ ለዓመታት የተከማቸ የህዝብ ብሶት ውጤት እንጂ የአንድ ጀምበር ስሜታዊነት የወለደው ክስተት አይደለም፡፡ አገሪቱን በመምራት ላይ ያለው መንግስት ለህዝብ ጥያቄ ዋጋ ያለመስጠትና የስልጣን ምንጭ የሆነውን ህዝብ የመናቅ ባህሉ ስር የሰደደ በመሆኑ ምክንያት ህገ-መንግስታዊና ሰብዓዊ መብቱን በሰላማዊ መንገድ የጠየቀን የህብረተሰብ ክፍል እንኳ እንደጠላት ሲመለከትና በሽብርተኝነት ሲፈርጅ ቆይቷል፡፡ ለዚህም መንግስት የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችን የእምነት ነፃነት ጥያቄ ያስተናገደበት መንገድ አንዱ ዋቢ ማሳያ ነው፡፡ የፍትህ ስርዓቱም ከፖለቲካ ውሳኔ ነፃ ያልሆነና አንዱ የመንግስት መጨቆኛ መሳሪያ ለመሆኑ በኮሚቴያችን አባላት እና በተባባሪዎቻችን ላይ የተላላፈው ኢ-ፍትሃዊ የፍርድ ውሳኔ በዋነኛ አስረጂነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ስለሆነም መሰል የህዝብ ጥያቄዎች በኃይል በመታፈናቸው፣ ፍትህ በመጓደሉና የዜጎች መብቶችና ነፃነቶች እጦት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ ህዝብ ስርዓቱን በመቃወም አደባባይ እንዲወጣ ተገድዷል፡፡

ይህንን ታሪካዊ ክስተት በብስለት ማስተናገድ በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ አገራት የሚገኙ ሁሉም የአገራችን ዜጎች ኃላፊነት ነው ብለን እናምናለን፡፡ በጥላቻና በበቀል ፖለቲካ ስትታመስ የኖረችዋ አገራችን ያሉባት ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ተቀርፈው የዜጎች ነፃነትና መብት የሚከበርባት፣ ዜጎች ተፈቃቅደውና ተከባብረው የሚኖሩባት፣ እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት፣ እንዲሁም የህግ የበላይነት የሰፈነባት የበለፀገች አገር ትሆን ዘንድ የአገራችን ህዝቦች ያነሷቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ሊያገኙ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል መንግስት የስልጣን ምንጭ የሆነውን ህዝብ ድምፅ በአፈሙዝ ለማፈን መሞከር ውጤት እንደማያስገኝ ሊረዳና ነፃነትን የተጠማ ህዝብ ዓላማውን ከማሳካት የሚያግደው አንዳችም ምድራዊ ኃይል እንደሌለ ሊገነዘብ ይገባል፡፡ ሰላምን በማስከበር ሽፋን ህዝብ ላይ ወታደራዊ ጥቃት መፈፀም መፍትሄ ሊሆን እንደማይችልም ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ህዝብም መሰረታዊ ለውጥ በማያመጣ ማስታገሻ ምላሽ እንደማይታለል ሊረዳ ይገባል፡፡ ይልቁንም መንግስት ከግትርነትና ከፓርቲ ወገንተኝነት ተላቅቆ ከፍ ያለ አገራዊ ምልከታ ሊኖረውና ህዝቡ ያነሳቸው ጥያቄዎች ተገቢውን መፍትሄ ያገኙ ዘንድ ሚናውን በመወጣት ከታሪክ ተወቃሽነት ራሱን ሊያድን ይገባል እንላለን፡፡ በተጨማሪም በመንግስታዊ ተቋማት ውስጥ በሁሉም የስልጣን እርከን ላይ የሚገኙ ዜጎች ለአገርና ለወገን የሚጠቅሙ ተግባራትን በመፈፀም ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አደራ እንላለን፡፡

የሃይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች ከህዝብ ፍላጎት፣ ጥቅምና ደህንነት፣ እንዲሁም ከእውነት ጎን በመቆም ውጥረቱ በሰላማዊ መንገድ ይፈታ ዘንድ መንግስትን የመምከር፣ የህዝብን ድምፅ ያከብር ዘንድ የመገሰፅ፣ እንዲሁም ዜጎች ወንድማማችነታቸውንና አንድነታቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው የማስተማር ወቅታዊ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ይህንን ሃይማኖታዊና አገራዊ ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ሊጥሩ ይገባል እንላለን፡፡ የሃይማኖት መሪዎች ምግባር ይህን መምሰል ቢገባውም የሕገ-ወጡ መጅሊስ አመራሮች ግን በተለያዩ ጊዜያት መንግስት በህዝብ ላይ እርምጃ እንዲወስድ የሚያበረታቱ ፀብ አጫሪ አስተያየቶችን ሲሰጡ ተስተውለዋል፡፡ ነገር ግን እነኚህ ግለሰቦችም ሆኑ የሚሰጧቸው አስተያየቶች ህዝበ-ሙስሊሙን ፈጽሞ የማይወክሉ መሆናቸውን ሁላችንም የምናውቀው እውነታ ነው፡፡

## ውድ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ሆይ!

ላለፉት አምስት ዓመታት በህዝበ ሙስሊሙ የእምነት ተቋማት ውስጥ የመንግስትን ህግ-ወጥ ጣልቃ ገብነት በአደባባይ እየተቃወማችሁ እና የእምነት ነፃነታችሁን ለማስከበር በሰላማዊ መንገድ እየታገላችሁ ዛሬ ድረስ በፅናት ዘልቃችኋል፡፡ ለዚህ ልፋታችሁ ልዕለ-ኃያሉ ፈጣሪያችን ምንዳችሁን ያበዛላችሁ ዘንድ እንመኛለን፡፡

## ውድ ወገኖቻችን ሆይ!

ነፃነትና መብት በህዝብ እጅ ያሉ ውድ ሃብቶች ናቸው፡፡ እነዚህን ሃብቶች ተነጥቆ የተገፋ የትኛውም ህዝብ ስለ እኩልነቱ እና ስለእኩል ተጠቃሚነቱ በተግባር መረጋገጥ የመታገል ኃላፊነትና ሚናው በግንባር ቀደምትነት የራሱ ነው፡፡ ሰው በመሆናችን ብቻ የተጎናጸፍናቸውን ነፃነቶችና መብቶች ማስከበር የህልውና ጉዳይ በመሆኑ የእያንዳንዱ ዜጋ የነፍስ ወከፍ ኃላፊነት መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገራት የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በሙሉ አገራችን ኢትዮጵያ የዜጎች ነፃነት የተከበረባት፣ ፍትህ የሰፈነባትና እኩልነት የተረጋገጠባት አገር ትሆን ዘንድ ከመላው የአገሪቱ ዜጎች ጋር እጅ ለእጅ በመሆን ሚናችሁን መወጣት ለነገ የማይባል ኃላፊነታችሁ መሆኑን ለማሳሰብ እንሻለን፡፡ የሃይማኖትና የዘር ልዩነት ሳይገድበን ለፍትህ በአንድነት መቆም እንዳለብን የአላህ መልእክተኛ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰላም በእርሳቸው ይሁንና) አስተምረውናል፡፡ በተግባርም አሳይተውናል፡፡

## ውድ የአገራችን ህዝቦች ሆይ!

በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገራት የሚገኙ ምሁራንና የለውጥ አራማጆች /activists/ አገራችንን አሁን ካለችበት ውጥንቅጥ መታደግ የሚያስችል፣ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት የሚያሳትፍና የሚያግባባ የመፍትሄ አቅጣጫ ላይ ለመድረስ በአንድነት ሌት ተቀን መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ የፖለቲካ ልሂቃንም በፖለቲካ ዲስኩሮቻቸውም ሆነ በጋዜጣዊ መግለጫዎቻቸው የህዝብን አንድነትና ወንድማማችነት ከምንጊዜውም በበለጠ በተደጋጋሚ መግለጻቸውና ይቅርባይነትን መሰረት ያደረገ ፖለቲካ ማራመዳቸው እጅግ ጠቃሚ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በዚህም የበቀል፣ የጥላቻና የማግለል የፖለቲካ ባህልን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ግብዓት-መሬቱን ለመፈጸም ይቻላል የሚል ጥልቅ እምነት አለን፡፡

## ውድ የአገራችን ህዝቦች ሆይ!

ከየትኛውም ወገን የሚሰነዘሩ፣ ህዝብን ከህዝብ ሊያጋጩ የሚችሉ፣ አንድን የተለየ ብሄር ወይም ማህበረሰብ አጠቃላይ በሆነ መልኩ የሚያወግዙ፣ የሚያስገልሉና በእኩይነት የሚፈርጁ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳዎች አገርን አደጋ ላይ የሚጥሉ በመሆናቸው ይህን መሰል ሁኔታ እንዳይፈጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትም ጸረ-ህዝብ እና አፍራሽ አካሄዶች እንዳይፈጠሩ የመከላከል ስራቸውን ከመስራት እንዳይዘናጉ አጥብቀን እናሳስባለን፡፡

ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ ያለው ህዝባችን ለዘመናት የዘለቀ ወንድማዊ ትስስሩን ጠብቆ የበለፀገችና ለዜጎች ኑሮ ተመራጭ የሆነች ኢትዮጵያን እውን እንደሚያደርግ አንጠራጠርም፡፡ በዚህ አጋጣሚም ህዝባችን የዘርና የሃይማኖት ልዩነት ሳይገድበው አንድነቱን ላሳየበት፣ የአንዱ ጉዳይ የሌላውም መሆኑን ላስመሰከረበት ለዚህ ታላቅ ታሪካዊ ክስተት ያለንን አድናቆት ለመግለፅ እንወዳለን፡፡ በሂደቱም በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በሌሎችም የአገራችን ክፍሎች ህይወታቸውን ባጡ እና የአካል ጉዳት በደረሰባቸው ወገኖቻችን ምክንያት የተሰማንን እጅግ መራር ሐዘን እየገለጽን ለቤተሰቦቻቸው እና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መጽናናትን እንመኛለን፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ የዜጎች ነፃነት የተከበረባት፣ ፍትህ የሰፈነባት፣ እኩልነት የተረጋገጠባትና ዜጎች በሰላም የሚኖሩባት የበለፀገች አገር ትሆን ዘንድ ዘወትር በፀሎታችን እንድናስባት አጥብቀን አደራ እንላለን፡፡ አምላካችን ሆይ! እናት አገራችንን ኢትዮጵያን ነፃነት፣ ፍትህ፣ እኩልነትና ሰላም የሰፈነባት፣ ለሰው ልጆች መኖርያነት ተስማሚ፣ በቁሳዊም ሆነ ሞራላዊ ብልፅግናዋም ከዓለም አገራት ተጠቃሽ ታደርግልን ዘንድ አጥብቀን እንለምንሃለን! አሚን!

---

ግልባጭ፡- ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ሚዲያዎች በሙሉ